ydb#B B/@éC½ B/@rsïCÂ ?ZïC KLL mNGST db#B nU¶T Uz@È

DEBUB NEGARIT GAZETA OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES REGIONAL STATE

11ኛ ›mT q$_R 2 bdb#B B/@éC½ B/@rsïCÂ ?ZïC KLል Mክር b@T -ÆqE T yw 2 ደንብ 11th Year No 2
ሀêú መጋቢት 1 ቀን 1997 ዓም Hawassa,September16/ 200

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር የወጣ ደንብ ቁጥር **29/1997**

የጥብቅና አገልግሎት በሕግ ሙያ የሰለጠነና ሰፊ ልምድ ያለው፣ የፍርድ ቤት አሥራርን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የታማኝነትን፣ የቅንነትና የእውነተኛነት መንፈስን የተላበሰ ሰው ለሕግ የበላይነትና ለፍትህ መስፈን ከፍትህ አካላት ጎን በአጋዥነት የሚሰለፍበት ሙያ በመሆኑ፣

በክልሉ ፍ/ቤቶች ለመስራት የሚችሉ ጠበቆችን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ በተሟላ መልኩ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የጥብቅና ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን የሙያ ብቃት ደረጃ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር የተመጣጠነ ለማድረግ በሥራው ለመሰማራት የማየስፈልጉ መስፈርቶችን በግለጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፣

የክልሉን አስፈፃሚና ፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/95 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በክልሉ ፍ/ቤቶች ስለሚሠሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 29/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

A Regulation No. 29/2004 To Provide For the Licensing And Administration of Advocates Practicing Before Southern Nation Nationalities And Peoples Regional Courts.

WHERE AS, advocacy as a profession where in a person trained and experienced in law, full aware of judicial proceedings and dictated by the spirit of loyalty, Sincerity and genuinely and works in cooperation with the Judicial organs for the rule of law and prevalence of Justice,

WHERE AS, it is deemed essential to regulate exhaustively, the licensing and registration of advocates practicing before regional courts,

WHERE AS, it has be come necessary to provide explicitly, the criteria required for practicing advocacy with a view of harmonizing the professional competence of advocates with the services they render.

NOW THE REFORE, in accordance with article 56 of the regional state proclamation no. 64/2004 that provide for the definition of power and duties of executive and executing organs, it is here by declared as follows,

PART ONE

አንቀጽ **2** ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

1. “ክልል” ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ክልል ማለት ነው።
2. **“**ቢሮ” ወይም “ቢሮ ኃላፊ” ማለት የደቡብ ክልላዊ መንግሥት ፍትህ ቢሮ ወይም ፍትህ ቢሮ ኃላፊ ማለት ነው።
3. **“**ጠበቃ” ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው የሕግ ባለሙያ ነው።
4. **“**ፍርድ ቤት” ማለት የክልሉ ፍ/ቤቶችንና መሰል የዳኝነት አካላትን ያጠቃልላል።
5. **“**ደንበኛ” ማለት ስለራሱ ወይም ስለሌላ ሰው ጉዳይ ማንኛውንም የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት ከጠበቃ ጋር የተዋዋለ ወይም የጉዳዩን ፍሬ ነገር ለጠበቃ ያስረዳ ሰው።
6. **“**የጥብቅና አገልግሎት” ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ ፍ/ቤት ፊት ሊቀርብ የሚችል ማናቸውንም ዓይነት የውል ስምምነት፣ የድርጅት ማቋቋሚያ ወይም ማሻሻያ ወይም ማፍረሻ ሠነድ ወይም ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ሠነድ ማዘጋጀት፣ ሶስተኛ ወገኖችን በመወከል በፍ/ቤት ቀርቦ መከራከርንና ማናቸውንም ዓይነት የሕግ ምክር አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል።
7. **“**መዝገብ” ማለት ጠበቆች የሚመዘገቡበትና በቢሮው የሚጠበቅ ሪኮርድ ነው፤
8. **“**የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ” ማለት የሕግ ምክርና አስተያየትን በመስጠትና ሕግ-ነክ ሠነዶችን በማዘጋጀት ጠበቃውን የሚያግዝ ሰው ማለት ነው።
9. “የጠበቃ ረዳት” ማለት በጠበቃው ሥር በመሆን በጠበቃው የተዘጋጁ የክስ ማመልከቻዎችን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ቆይል የሚያስከፍት፤ ከፍርድ ግልባጮችን በማውጣት ለሚመለከታቸው ሰዎች የሚያደርስ ሰው ነው።
10. **“**ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
11. **“**ልዩ የጥብቅና” ማለት የሕብረተሰቡን ወይም የደንበኛውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ሲባል ያለምንም ክፍያ በፍላጎታቸው አገልግሎት መስጠት ለሚችሉ ሰዎች የሚሰጥ የፍቃድ ዓይነት ነው።

Article 2 Definitions

In this regulation, may be cited as the “Regional Courts practicing advocates licensing and Administration Regulation no 29004”

1. “Region” means Southern Nations Nationalities And Peoples Region.
2. Bureau” or” Head, Bureau” means Southern Nations Nationalities And Peoples Regional state Justice Bureau or Head of Justice bureau.
3. “Advocate” means a layer who is delivered advocacy license in order to render advocacy service
4. “Court” Means regional courts and quasi-judicial organs.
5. “Client” means a person who enters in to contracts with on advocate to obtain advocacy service with on advocate to obtain advocacy services for himself or for a third party or who tells the facts of the case to an advocate.
6. “Advocacy Service” means the preparation of contracts, memorandum of association, documents of amendment or dissolution, of same, or documents to be adduced in courts, litigation before courts on behalf of third parties, and includes rendering any legal consultancy services for consideration or with out consideration or for direct or indirect future consideration.
7. “Register” means a record where in advocates are registered and kept by the bureau.
8. “low clerk” is a person who assists
10. “Person” means any natural or juridical person
11. “Special Advocacy License” means types of Advocacy license issued to any Ethiopian who defends

the general interest all rights of the

አንቀጽ **4** የጥብቅና ፈቃድ ለመስጠት የመመዘኛ ነጥቦች

ለማንኛውም ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ከዚህ የሚከተሉት መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው።

1. በሕግ ትምህርት የሰለጠነ እና በሕግ ሙያ ሥራ ልምድ ያለው ኢትዮጵያዊ/ት፣
2. የሀገሪቱን ሕገች ጠንቅቆ የሚያውቅ፣
3. ለፍትሕ ሥራ አካሄድ መልካም ሙያዊ ሥነ-ምግባር ያለው፣
4. ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ

Article 4 Requirements for issuance of advocacy license.

The following requirements shall be fulfilled for all levels of advocacy license.

1. Education in law which is relevant to advocacy and related service.
2. Knows the basic law of Ethiopia
3. Whose codes of conduct is suitable for

አንቀጽ **7** አቃድ ስለመስጠት፤

1. የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ በአንቀጽ 5 እና 6/1/ መሠረት ተሟልቶ ውሣኔ ይሰጣል።

2. በፈቃዱ ላይ የሚጠቀሱት የሚከተሉትን ይጨመራል፤

   ሀ/ የጠበቃው ሙሉ ስምና ዜግነት

   ለ/ መደበኛ የመኖሪያና የሥራ አድራሻ

Article 7. Issuance of license

1. Where the bureau finds that the application made for a license is in full complication made for a license is in full compliance with the provisions of Article 5 and 6 (1) of this regulation, it shall render its decision.
2. The license shall include the

አንቀጽ **9** የጥብቅና ፈቃድ ዕድሣት

1. የጥብቅና ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት።
2. ፈቃድ ለማሣደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃድ የሚያገለግልበት የአንድ ዓመት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት።
3. አመልካች በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣው መመሪያ መሠረት የማሳደሻ ክፍያ ይከፍላል።

Article 9 Renewal of Advocacy License

1) A license shall be renewed annually

2) An application of renewal of license shall be submitted one month before the expire of the one year period for which it is issued.

አንቀጽ **10** የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች፤

በዚህ ውስጥ የሚሰጡ የሚከተሉት ሰባት የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች

1. በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ በመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የተመረቀ፤ በሙያው ቢያንስ የ 2 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም
2. በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀ በሙያው ቢያንስ 4 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው።

አንቀጽ **12** የሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መሠፈርቶች የሚሊ ሰው በከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፊት ቀርቦ ለመከራከር የሚያስችል የ 2 ኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ የሰጣል።

1. በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ ዲፕሎማ

1. Where he has a degree in law form a legally recognized educational institution and has a minimum of two years relevant experience

2. Where has a diploma in law from a legally recognized educational institution and has minimum of four years relevant experience.

ለ/ ከሚወክለው የሕብረተሰብ ክፍል ወይም ደንበኛ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይቀበል፤

ሐ/ ፀባዩ ይህን ኃላፊነት ለመቀበል ተስማሚ የሆነ፤

መ/ ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፤

2. የጥብቅና ፈቃድ ያለው ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፁትን የሚያሟላ ከሆነ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ሳያስፈልገው አገልግሎት መስጠት ይችላል። ነገር ግን ይህን አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ለቢሮው ማሳታወቅ አለበት።

3. ቢሮው ስለ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ በፈቃዱ ስለሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት የአገልግሎት ጥራት እና ስለባለፈቃዶቹ ሥነ-ምግባር ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 14 ቃለ መሃላ ስለመፈፀም

ማንኛውም ፈቃድ የሚሰጠው ጠበቃ የሚከተለውን ቃለ መሃላ በጽሑፍ ያረጋግጣል።

እኔ ..... ዛሬ ..... ቀን .....ዓ/ም ከቢሮው

b) Who may not receive any kind of reward form a section of society of client

c) Whose character is suitable for shouldering such responsibility

d) Who is not convicted and sentenced in an conduct

2. Any person who has an advocacy license and meets the requirements specified in the provisions of sub-article (1) of this Article may render advocacy services with out as special advocacy license. However, he shall notify the

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈቃድን የመለሰ ጠበቃ ፈቃዱን እንዲመልስ ያስገደደው ምክንያት እንዳበቃ ወይም እንደተወገደ ከሥራው ተለይቶ በቆየበት ጊዜ በሥነ-ምግባር ጉድለት ሊያስጠይቀው የሚችል ጥፋት ያለመፈፀሙን ማስረጃ በማቅረብ ፈቃዱን ሊወስድ ይችላል።

አንቀጽ 16 ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

1. ይህን ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን የተላለፈ ጠበቃ እንደሁኔታው ፍቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንድ ፈቃዱ ሊሰርዝ ይችላል።

ሀ/ ፈቃዱ የተገኘው በማታለል ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም

2. An advocate who has returned his license in accordance with sub-article (1) of this article may, re-take same upon termination or removal of the cause which compelled him to return his license, provided that he has not committed any fault which would make him liable for breach of discipline.

Article 16 Suspension or Revocation of license

1. A license may be suspended or

ሠ/ ከጥቅብና ሙያና በታገደበት ወቅት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት መስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

ረ/ ከጥብቅና ሙያ ጋር በግልጽ የሚጋጭ ወይም የማይጣም ተጨማሪ ሥራ ሲያከናውን የተገኘ እንደሆነ፣

ሰ/ በራሱ ወይም በሌላ ጠበቃ አገናኝ አማካይነት ሥራ ለማስገኘት ገንዘብ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል።

ሀ/ ያለ በቂ ምክንያት ፈቃዱን በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 መሠረት ያላሳደሰ እንደሆነ፤

ለ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ ወይም የጠበቃ ረዳት አድርጎ ያሠራ እንደሆነ፤

e) Where he is found practicing advocacy while suspended

f) Where he carries cut additional activity which is obviously conflicting or in consistent with his profession

g) Where he gives or attempts to give many which is obviously conflicting or in consistent with is profession

3. Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this article the

አንቀጽ **17** ስለመመዝገብ

1. ፈቃድ የተሰጠውን ጠበቃ ስምና ዜግነቱ፤ የፈቃድ ዓይነቱ፤

አንቀጽ **18** ከጠበቃው ጋር የሚሰሩ ሰዎችን ስለመመዝገብ፤

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት በሥራው የሚያግዙትን የሕግ ጉዳይ ፀሐፊዎች፤ የጠበቃ ረዳቶች፤ ፀሐፊዎች የሌሎች ሠራተኞች ስም እና የሥራ ኃላፊነት ቢሮው ለዚህ ጉዳይ ለመደበው ባለሥልጣን በጽሑፍ በማሳወቅ ያስመዘግባል።
2. ማንኛውም ጠበቃ ከቢሮ ኃላፊው ወይም በእርሱ ከተወከለ ባለሥልጣን ፈቃድ ሳይገኝ፥-
   ሀ/ ከመዝገቡ ስሙ የተፋቀን፤
   ለ/ ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት የታገደን፤
   ሐ/ በዲሲፒሊን ጥፋት በመሥሪያ ቤቱ የተባረረ ሰው
   መ/ ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከስሶ የተፈረደበትን ወይም
   ሠ/ በመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ የሚሠራን ሰውን፤ በጠበቃ ረዳትነት ወይም በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት መቅጠር አይችልም፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሕግ ትምህርት ወይም ሥልጠና እና ልምድ የሌለው

Article 18 Registration of persons working with the advocate

1. Any advocate or la law firm shall notify in writing to an official assigned,, by the Bureau for registration of the names and responsibilities of secretary typists, law clerks, assistant advocates and other employees working under his supervision.
2. Any advocate may not,, without a prior consent of the head of Bureau or an official designated by him, employ the following persons as assistant advocate or a law clerk.
   a) A person whose name is

2. በዚህ ደንብ መሠረት የሚቋቋመው ድርጅት የንግድ ማሕበር ያልሆነ ኃላፊነቱ ለተወሰነ ማሕበር ይሆናል።

3. በቢሮ ወይም እርሱ የወከለው ባለሥልጣን የድርጅት ማቋቋሚያ ሠነዱን ከመረመረ በኋላ የድርጅቱ መቋቋም፤

   ሀ/ የጠበቆችን የሥነ-ምግባር ደንብ የማይጥስ፤

   ለ/ የደንበኞችን ወይም የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ሲያምን ስሙን በመዝገብ አስገብቶ ፈቃድ ይሰጠዋል።

4. ስለጥብቅና ሙያ ድርጅት ፈቃድ አሰጣጥ እና ከዚህ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በዝርዝር ይወሰናል።

ክፍል ሶስት

አስፈፃሚ አካላት

አንቀጽ **20** የቢሮው ሥልጣንና ተግባር ቢሮው፡-

1. የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፤ ጠበቆችን ይመዘግባል፤ የጥብቅና ፈቃድን ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

2. በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የተወሰነውን

2. The nature of the firm shall be non-business organization, the liability of witch is unlimited

3. The Bureau or n official designated by it shall, after examining the memorandum of association of the firm enter its name in the registry and issue license where it believes that the formation of the firm;

   a) Does not breach the advocates code of conduct:

   b) Is not prejudicial to the interests of its clients or to third parties

4. Particulars as for the licensing of law firms and related matters shall be stipulated in directive to be issued in accordance with this regulation.

አንቀጽ **21** የክክሉ ጠበቆች ዲስፒሊን ጉባዔ

1. የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የጠበቆች የዲሲፒሊን ጉባዔ ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ ይኖራል።
   ሀ/ በቢሮ ኃላፊው የሚወከሉ ሶስት ተወካዮች
   ለ/ በጠበቆች ማሕበር የሚወከል አንድ ተወካይ
   ሐ/ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚወከል አንድ ተወካይ
2. የጉባዔው ሰብሣቢ የሥራ ዘመን 3 ዓመት ሲሆን የሌሎች አባላት 3 ዓመት ነው፤
3. የጉባዔው ሰብሣቢ ከአባላቱ ውስጥ በቢሮ ኃላፊው ይሰየማል።

አንቀጽ **22** የክልሉ ዲስፒሊን ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

1. የዲሲፒሊንን ጉዳይ በሚመለከት ጉባዔው ከዞን፤ በመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ይግባኝ ሲቀርብለት አይቶ ይወስናል። ውሣኔው ከታች የተሰጠውን ውሣኔ የሚያሻር ከሆነ የውሣኔ ሃሣቡን ለፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ያቀርባል። የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።
2. የጠበቆች የሥነ-ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለቢሮ ያቀርባል።

Article 21 Regional Advocates Disciplinary council

1) There shall be advocates disciplinary council hereinafter, referred to as "the council" composed of the following members

   a) Three representatives of the Bureau

   b) A representatives of the advocates association

   c) A representative of the regional supreme court

2) The term of office of a member shall be two years and the chair person of the council shall be three years

3) The chair person of the council shall be designated by the head of bureau from among the members there of.

Article 22 Powers and Duties of

አንቀጽ **23** የጉባዔው ስብሰባ

1. ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል።
2. ከጉባዔው አባላት አብዛኞቹ ከተገኙ ምልዓቱ ጉባዔ ይሆናል።
3. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው የደገፈው ሀሣብ ይወሰዳል።
4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ **24** የቢሮ ኃላፊ ሥልጣን፤

1. የቢሮ ኃላፊ በአንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በአንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት ከጉባዔው ወይም ከቦርድ የቀረበውን የውሣኔ ሃሣብ ከመረመረ በኋላ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል።
2. ጉባዔው ወይም ቦርዱ በአግባቡ ያላጣራው ወይም ያላጤነው ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ይኸው ተጣርቶ ወይም ተገናዝቦ እንዲቀርብለት ለኮሚቴው ወይም ለጉባዔው ለአንድ ጊዜ መመለስ ይችላል።

አንቀጽ **25** የዞን ጠበቆች ዲስፒሊን ጉባዔ

ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. በዞን ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ዋና መምሪያ ኃላፊ የሚወከል ሁለት ተወካይ

Article 23 Meeting of the council

1. The council shall conduct meeting as frequently as required
2. There shall be a quorum where more than half of the members are present
3. The term of office of a member of the committee shall be two years and
4. Decision of the council shall be {assed by a majority vote of members present at a meeting incase of tie, however, the chair person shall have a casting vote
5. Without prejudice to the Article the council may draw up its own rules or procedure

Article 24 Powers of the Head of Bureau

1. The head of Bureau shall, after considering the recommendation

3. ከጠበቆች ማህበር የሚወከል አንድ ተወካይ
4. ከዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አንድ የሕግ ባለሙያ

አንቀጽ **26** የዞን የዲስፒሊን ጉባዔ ሥልጣንና ተግቦር፡-

1. ይህንን ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣው የሥነ-ምግባር መመሪያ ወይም ደንብ በመተላለፍ በጠበቃ ላይ የሚቀርብ ክስን ተቀብሎ ያጣራል፤ ይመረምራል፤
2. በጠበቃው ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የሚያበቃ ማስርጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ጠበቃው መልሱን በ 30 ቀን ውስጥ አንዲያቀርብ በመጥሪያው ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃው ይልካል፤
3. በጠበቃው ላይ የቀረበውን ክስና ማስርጃ እንዲሁም በጠበቃው በኩል የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፤
   ሀ/ ክሱ ተገቢ ካልሆነ ወይም በበቂ ማስረጃ ካልተደገፈ ክሱን በመሠረዝ ጠበቃው እንዲሰናበት፤
   ለ/ ክሱ ተገቢና በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ እንደጥፋቱ ክብደት፡-
   1. ጠበቃው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ጠበቃው
   2. ጠበቃው ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከሥራው እንዲታገድ፤
   3. ከብር 10,000 /አሥር ሺህ/ ያልበለጠ ቅጣት እንዲጣልበት፤
   4. ፈቃዱ ተሰርዞ ስሙ ከመዝገብ እንዲፋቅ፤

3. A representatives of the advocates association
4. A representative of the zonal high court,

Article 26 Powers and duties of the zonal council the council

1. Shall investigate a charge brought against an advocate violating the provision of this regulation or the advocates code of conduct or directives issued in accordance with this regulation.
2. Shall, where it ascertains that there is adequate, evidence to entertain the charge, send the charge to the advocate, notifying him in the summons to appear with his reply with in 30 days
3. Shall submit, after examining the charge brought and evidence

5. ተገቢነው ያላቸውን ሌሎች ውሣኔዎችን ሊሰጥ ይችላል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተገቢውን ውሣኔ እስኪወሰድ ድረስ የጥብቅና ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል።
7. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጠበቃው ላይ የሚጣለውን የቅጣት መጠን ለመወሰን የወንጀል ሪኮርድ፤ የጠበቃውን የግል ማሕደር ወይም ሌላ ተመሣሣይ ማስረጃ መስማትና መመርመር ይችላል።።
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ለ መሠረት የተሰጠውን ማንኛውም ውሣኔ በጠበቃው የግል ማሕደር ውስጥ እንዲመዘገብ ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋል።
9. የጠበቆችን የሥነ-ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለቢሮው ሃሣብ ሊያቀርብ ይችላል።
10. የቀረበውን ማንኛውንም ክስ ክሱ በቀረበ ከሶስት ወር ባለበለጠ ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት አለበት።

4. በአካባቢ ፍትህ ማስተባበሪያ የሚሠሩ ጠበቆች ጉዳይ በሚገኙበት ዞን ፍትህ መምሪያ በኩል ይታያል።
5. በልዩ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የሚሠሩ ጠበቆች ጉዳይ በአንራባች ዞን ፍትህ መምሪያ በኩል ይታያል።

አንቀጽ **27** የጉባዔው ስብሰባ

1. ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል።
2. ከጉባዔው አባላት አብዛኛዎቹ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።
3. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው የደገፈው ሀሣብ ይወሰዳል።

5. To give such other appropriated decisions
6. May temporarily suspend the license until such time that an appropriate decision is given as per sub-Article (3) of this article
7. May examine, where deemed necessary the antecedents and personal tile of the advocate or any other similar evidences in determining the magnitude of the penalty to be imposed
8. Shall cause the recording of any decision to the Bureau given as per sub-Article 3(6) of this article in to the personal file of the advocate.
9. Shall undertake studies and submit recommendation to the Bureau on ways of enhancing and the observance of professional conduct
10. Shall render decision on any charge with in a period not exceeding three months;

አንቀጽ **28** የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና አዘጋጅ፣ የችሎታ ብቃት መለኪያና የፈቃድ ገምጋሚ ቦርድ

1. ተጠሪነቱ ለቢሮው የሆነ የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና አዘጋጅ፣ የችሎታ ብቃት መለኪያና የፈቃድ ገምጋሚ ቦርድ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ ይሆናል።

   ሀ/ የቢሮው ሶስት ተወካዮች

   ለ/ የጠበቆች ማሕበር ተወካይ

   ሐ/ የጠቅላይ ፍ/ቤት ተወካይ

   መ/ በቢሮ ኃላፊ የሚመረጡ ሌሎች ሁለት አባላት

2. የአንድ አባል የሥራ ዘመን ለአራት ዓመት ሲሆን የቦርዱ ሰብሣቢ በቢሮ ኃላፊ ይመረጣል

3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ቢኖርም የሰብሣቢው የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ነው።

አንቀጽ **29** የቦርድ ሥልጣንና ተግባር ቦርዱ

1. በቢሮ ኃላፊ ወይም በእርሱ ከሚወከል ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ማመልከቻው እንደቀረበ የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል።።

2. የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፤ ለማለፊያ የሚያበቃውን ነጥብ ይወስናል፤ የፈተናውን ውጤት ለቢሮ ኃላፊው ወይም በእርሱ ለሚወከል ባለሥልጣን አቅርቦ ሲፀድቅ ውጤቱን በይፋ ያስታውቃል።

3. የአመልካቹን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዲከላከል ለቢሮ ኃላፊው ውሣኔው ሀሣብ ያቀርባል፤

Article 28 Advocacy Entrance exam setting and competence certifying and license evaluating Board

1. There shall be Advocacy entrance exam setting, competence certifying and license evaluating Board, here in after referred to as "the Board" composed of the following members

   a) Three representatives of the Bureau
   b) A representative of Advocates Association
   c) A representative of regional supreme court.
   d) Two other members nominated by the head of Bureau

2. The term office of a member shall be four years and the chairman of the Board shall be nominated by the head of Bureau.
3. Not with standing sub-Article (2) of this article the tem office of chair man of the board shall be five years

4. አመልካቹ ለፍትህ ሥራ አካሄድ የሚስማማ የሥነ-ምግባር ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ መመርመር ይችላል። የሥነ- ሥርዓት መመሪያን አዘጋጅቶ ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል።

አንቀጽ **30** በቢሮ ኃላፊ ውሣኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

1. ቢሮ ኃላፊው የሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በውሣኔ ቅር የተሰኘው ወገን ውሣኔው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል።
2. ፍርድ ቤቱ ወደፍሬ ነገር ሳይገባ በሕግ ጉዳይ ላይ ውሣኔ በመስጠት ጉዳዩን ለቢሮ ኃላፊ ይመልሰዋል።
3. የቢሮ ኃላፊ ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ቢሮ ኃላፊ የፍርድ ቤቱን ውሣኔ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደገና እንዲታይ ያደርጋል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ **31** የጠበቃው ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ፡-

1. ይህን ደንብና በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣውን መመሪያ እና የሚሰጡትን ትዕዛዞችና ውሣኔዎች ማክበር፤

4. May cause to production of any witness or evidence and examine same with a view to a ascertaining the suitability of the advocates character in assisting the administration of justice Issue and submit to the head of Bureau is own rules of procedure and implement same up on approval

Article 30 Appeal Against the decision of the head of Bureau

1. The person who is aggrieved by the decision of the head of Bureau may, where the decision has an error of law, appeal to the regional supreme court with in thirty days from receipt of such a decision
2. The court shall decide on the question of law, with out going into the merit, and shall return same to the head of Bureau
3. If the decision of the head of Bureau has an error of law, the head of bureau shall review the case on the basis of the decision of court

2. ከደንበኛው ለሚቀበለው ማንኛውም ዓይነት ክፍያ ደረሰኝ የመስጠት፤
3. በደንበኞቹ ላይ በሙያው ለሚያደርሰው የፍትሐብሔር ጥፋት የጉዳት ካሣ እንዲሆን በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት መድህን መግባት፤

ፈቃድ ሲያወጣ፤ ሲያድስና ሲተካ ይህን ደንብ መሠረት አድርጎ በሚወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈለግበትን የፈቃድ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ **32** ቅጣት

በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጥብቅና ፈቃዱን ሳያሳድስ የጥብቅና አገልግሎት የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ፤ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ 199/1992 አንቀጽ 31 ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ **33** የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የክልሉ ጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ጠበቃ በነበረበት ደረጃ ፈቃዱን ይዞ ይቀጥላል። ነገር ግን ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የ3ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 እና 12 የተገለፁትን መስፈርቶች ሲያሟሉ ደረጃቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ።
2. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ውሣኔ ያላገኙ ወይም በአቤቱታ ደረጃ ያሉ የዲሲፕሊን ጉዳዮች በዚህ ደንብ መሠረት ይፈፀማል።

2. Give a receipt in respect of any consideration he receives from his client
3. Have an insurance policy, in accordance with sub-article (1) of Article (8) with a view to redressing any civil injury or harm to be incurred by his clients, due to his professional default

   Pay the fees required, in obtaining, renewing and replacing a license, by the directives to be issued in accordance with this regulation

Article 32 Penalties

Any person who renders or attempts to render advocacy service with out having obtained a license or renewing his license in accordance with this regulation, Article 31 of the federal court advocates licensing and registration proclamation no, 199/2000 shall be applied.

Article 33 Transitory Provisions

1. Any advocate who has advocacy license before this regulation has been issued shall render advocacy

አንቀጽ **34** ስለተሻሩ ሕጐች

ስለጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና የጠበቆች አስተዳደር ደንብ

1. ቁጥር 3/1991 በዚህ ደንብ ተሽሯል።
2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ **35** ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ከፀደቀበት መጋቢት 1 ቀን 1997 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዋሣ

ኃይለማሪያም ደሣለኝ

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ርዕሰ መስተዳድር

Article 34 Repealed laws

1. Advocacy licensing and administration regulation no 3998, is here by repealed.
2. Any law in consistent with the provisions of this regulation may not apply to matters covered under this regulation

Article 35 effective date

This regulation shall enter in to force as of 16th day of September, 2004

Done at Awassa,
This 16th day of, 2004
Hailmariam Desalegn
Chief-Executive of the Southern Nations, Nationalities and People regional state.

